ጋዜጣዊ መግለጫ

የአሜሪካ ኤምባሲ
አዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ
2017/ 38

ለበለጠ መረጃ በ011-130-7033 ይደውሉ
http://et.usembassy.gov ይጎብኙ

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) ለ25,000 ሰዎች አገልግሎት የሚሰጥ የጤና ማዕከል ገንብቶ አስረከበ

ጉለም ደጀን፤ አማራ ክልል፤ ኢትዮጵያ፤ ጥቅምት 27, 2010 ዓ.ም. ፤- የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) አዲስ ያስገነባውን የጤና ማዕከል በዛሬው ዕለት ለአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ቢሮ በይፋ አስረከበ፡፡ አዲስ የተገነባው የጤና ማዕከል በጉለም ደጀን እና አካባቢው ለሚኖሩ ከ25,000 በላይ ሰዎች አገልግሎት ይሰጣል፡፡

የአሜሪካ መንግሥት የጤና ክብካቤን በማሻሻል ረገድ ከኢትዮጵያውያን ጋር የረዥም ጊዜ የጠበቀ ታሪካዊ ትስስር አለው፡፡ ጤናማ ኢትዮጵያ ለጤናማ ዓለም ቁልፍ እንደሆነች እናምናለን፡፡ ኢትዮጵያውያን የተሻለ ነገን እንዲያሳኩ የምናደርገው ጥረት፤ የሀገሪቱን የጤና አቅም ለማጠናከር የምናደርገው ትስስር ቁልፍ አካል ነው፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID) የጤና፤ ኤድስ፤ ስነ-ህዝብ እና ስነምግብ ቢሮ ምክትል ሃላፊ ሶፊያ ብሪዊር በጤና ማዕከሉ የርክክብ ስነስርዓት ላይ ሲናገሩ፡ “ይህ የጤና ማዕከል የክትባት፤ የወሊድ፤ የኤድስ ክብካቤ እና ህክምና አገልግሎቶችን ጨምሮ ሌሎች ሕይወት አድን የጤና አገልግሎቶችን ይሰጣል” ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ የጤና መሠረተ ልማት ፕሮጀክት አካል የሆነውና በአሜሪካ ፕሬዝዳንት የአስቸኳይ ዕቅድ ለኤድስ ድጋፍ (PEPFAR) የገንዘብ ድጋፍ የተገነባው የጤና ማዕከል፤ ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ወይም የቫይረሱ ተጠቂዎችን ጨምሮ፤ አስፈላጊ የሆኑ የጤና አገልግሎቶችን ለአካባቢው ማኅበረሰብ ይሰጣል፡፡ ፕሮጀክቱ፤ ኢትዮጵያ በዋና ዋና ክልሎች የጤና መሠረተ ልማቶችን በመገንባት የኤች አይ ቪ ወረርሽኝን ለመቆጣጠር የምታደርገውን ጥረት በመደገፍ፤ ነፍሰ ጡር ሴቶች የወሊድ እና ኤች አይ ቪ በደማቸው ያለባቸው ሰዎች ፀረ-ኤች አይ ቪ መድሃኒት በንጹህ እና ደህንታቸው አስተማማኝ በሆኑ የህክምና ክፍሎች ማግኘት ያስችላቸዋል፡፡

ማዕከሉ በPEPFAR የገንዘብ ድጋፍ በUSAID እየተገነቡ ከሚገኙ 22 የጤና ማዕከላት 13ኛው ሲሆን፤ በመገንባት ላይ ያሉት ቀሪዎቹ ዘጠኙ ማዕከላት እ.አ.አ. በ2018 ውስጥ ይጠናቀቃሉ፡፡ USAID በተጨማሪም፤ እ.አ.አ. በ2016 ግንባታው ለተጀመረው እና እ.አ.አ. በ2018 ለሚጠናቀቀው የብሔራዊ የደም ባንክ ህንፃ ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ የልማት ድርጅት (USAID)፤ በኢትዮጵያ የጤና መሠረተ ልማት ፕሮጀክት በኩል፤ መድሃኒት እና ሌሎች የጤና ቁሳቁሶችን ለማከማቸት እና ለማሰራጨት የሚረዱ አስር የመድሃኒት ማከማቻ መጋዘኖችን የገነባ ሲሆን፤ ለተጨማሪ አስር የጤና ክብካቤ ማዕከላት የእድሳት አገልግሎት አድርጓል፡፡ እንደ አንድ የPEPFAR ድጋፍ ተጠቃሚ ሀገር፤ ኢትዮጵያ በUSAID፤ የበሽታዎች መከላከል እና መቆጣጠር ማዕከል (CDC)፤ የመከላከያ

ሚኒስትር (DoD)፤ የሰላም ጓድ እንዲሁም የውጭ ጉዳይ መሥሪያ ቤት አካል የሆነው ስነ-ህዝብ፤ ስደተኞች እና ተፈናቃዮች ቢሮ በሚመራው የዘርፍ አቀፍ የኤች አይ ቪ መርኃ-ግብር ድጋፍ ተጠቃሚ ናት፡፡ እ.አ.አ ከ2005 ጀምሮ፤ የአሜሪካ መንግሥት በPEPFAR በኩል ባደረገው ድጋፍ፤ በኢትዮጵያ አዲስ የቫይረሱ ተጠቂዎችን ቁጥር እና ከኤድስ ጋር ተያያዥ የሆነ ሞትን በትንሹ በ50 በመቶ እንዲቀንስ አስችሏል፡፡

###